

# ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር እንዴት እንነግራቸዋለን

# መግቢያ

ህይወት ጉዞ ነው። እግዚአብሔር ይወድሀል፤በዚህ በህይወት ጉዞ ውስጥ ስኬታማ እንድትሆን ይፈልጋል።ስኬት አንተን ጨምሮ በማንኛውም ሰው ህይወት ውስጥ አስደናቂውን የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትህ በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም ይወሰናል።በመረጥከው መንገድ ላይ በመሆን፤በዘለዓለማዊ መንግስቱ ውስጥ የተትረፈረፈውን በረከት እየተካፈልክ ልትፈጽም ትችላለህ ወይም በአንጻሩ ማለቂያ በሌለው ቅዠት ውስጥ ትኖራለህ።ብሩህ የሆነውን መንገድ መርጠህ የእግዚአብሔርን ዓላማ ትፈጽም ዘንድ በየዕለት ህይወትህ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ይኖርብሀል።ለዚህ ነው ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አንተን ለመርዳት የተዘጋጀው።

እያንዳንዱ ሦስት የትምህርት ክፍሎች አሉት: {1}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤ {2} መሠረታዊ ጥያቄዎች፤እና {3}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ ወይም ተግባራዊ ስራዎች ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማወቅ እንድታድግ ይረዱሀል።መሠረታዊ ጥያቄዎች ደግሞ በምታውቀው የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንድትኖር ይረዳሀል።የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ የቃሉን እውነት በልብህ እንድትሰውር ይረዳሀል።የተግባር ስራው የተማርከውን ሁሉ በሚገባ ተግባራዊ እንድታደርገው ይረዱሀል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ቃል እውነት ለሌሎች እንዴት ማካፈል እንደምትችል መማርህ አንዱ እሱን በማወቅ የማደግ አካል ነው።ሰዎች የምትማረውን በሚገባ እንድትተገብረው ይረዳሀል።ስለ እግዚአብሔር እና የምስራቹን ወንጌል ለሌሎች እንዴት ማካፈል እንደምትችል በማወቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች ጋር ትስማማለህ።እንዲሁም እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ውስጥ ያገኘኸውን የራስህን ታሪክ እንዴት እንደምትጽፍ እና ክርስቶስን የመዋጀት መልዕክት እንዴት ለዓለም እንደሚደርስ ትማራለህ።ሌሎች እግዚአብሔርን በማወቅ እንዴት እንደሚያድጉ ለመርዳት የምታገኘው መረዳት አንዱ የዚች አነስተኛ መጽሐፍ አካል ነው።

እያንዳንዱን ትምህርት በጸሎት ጀምር።መልሶቹን በራስህ አገላለጽ ጻፋቸው።በተገለጠልህ እውነት በሚገባ ትመላለስ እና ትኖር ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ። እግዚአብሔር እሱን በማወቅ ይባርክህ።

<u>ማስታወሻ</u>: አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መደበኛ ትርጉም መጠቀም ለዚህ የስልጠና አነስተኛ መጽሐፍ የተሻለ ነው።

# ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መናገር
# ትምህርት 1
## ማጠቃለያ

የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፤ አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).

**የዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ዓላማ:** እግዚአብሔር ማንኛውም ሰው እሱን በማወቅ እንዲያድግ እና በህይወቱ የሱን ዓላማ እንዲፈጽም ይፈልጋል።ይህ በእርግጥ እንዲሆን እሱን በማወቅ የሚያድጉ ሰዎች ለእሱ መኖር እና ስለ እሱ ለሌሎች መናገር አለባቸው።የዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ዓላማ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ታደርግ ዘንድ አንተን ማስታጠቅ ነው።
ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች ስለመናገር የመማር ዓላማው በየዕለት ህይወትህ ለምታገኛቸው ሰዎች ስለ እሱ መናገር እና ህይወታቸውን ለኢየሱስ ሊሰጡ የወሰኑትን ደግሞ ከእሱ ጋር ያላቸውን ህብረት በይበልጥ ይጠነክር ዘንድ መሰረት ለመጣል ነው።
ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር እንናገር ዘንድ የሚጠቅሙን አንዳንድ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው:
ጸሎት
ሰዎች በሚያስፈልጋቸው ነገር መርዳት
የምናገኛቸውን ሰዎች ጓደኛ ማድረግ

.

**ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ለመናገር የምናደርገው ዝግጅት የሚከተሉትን ያካትታል:**
*ሀ. ልባችንን እና ህይወታችንን ዝግጁ ማድረግ።*
1. እግዚአብሔርን በማወቅ ታድግ ዘንድ እና በህይወትህ የሱን ዓላማ እንድትፈጽም እራስህን አስገዛ።
2. ሁልጊዜ በመስቀሉ ስር ሁን (ከታች ያለውን ምስል ተመልከት). የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትህ ለመፈጸም እንዳትችል የሚደርግህን ነገሮች ከህይወትህ ውስጥ ለማስወገድ ፈቃደኛ ሁን።
እግዚአብሔርን እያወቅህ እንድታድግ በሚያስችሉህ ነገሮች ተካቸው።



ሀ. በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ጊዜህን በማሳልፍ እግዚአብሔርን በማወቅ እደግ።እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ዓላማ እና እንዴት እንደምትፈጽመው እወቅ።
(1) (ኤፌ 3:4) አንብብ
(2) (2 ጢሞ 2:15) አጥና
(3) (መዝ l) አሰላስል
(4) (መዝ ll9: ll) አስታውስ
(5) (ዕንባ 2:2) ጻፍ
(6) (ሮሜ 6:17-18) ኑረው
(7) (1 ዮሐ 1:1-3) ለሌሎች አካፍለው

ለ. ጸልይ።በየቀኑ ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች ትናገር ዘንድ ጸልይ:
(1) የሚያስፈልጉህ ነገሮች
(2) በየዕለት ህይወትህ የምታገኛቸው እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች የሚያስፈልጋቸው ነገሮች
(3) ሌሎች የኢየሱስ ተከታዮች የሚያስፈልጋቸው ነገሮች
(4) ስለ ኢየሱስ ለመናገር የምትመርጠው ቦታ እና ሰዎች

**ማስታወሻ: መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና እና ስንጸልይ ለማደግ አንዱ ውጤታማ መንገድ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ ነው።ተጨማሪ መግለጫ ሀን ይመልከቱ**

ሐ. በየዕለቱ እግዚአብሔርን እያወቁ ለማደግ እና የእሱን ዓላማ በህይወታቸው ለመፈጸም ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር ዋል።ጸልይ፣ዘምር፣መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ እንዲሁም ከሌሎች ጋር በመሆን ተካፈል።

መ. በየእለቱ የምታገኛቸውን ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ማካፈል ትችል ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ እና እንዲመራህ ጸልይ።እንዲሁም በሰዎች ፊት ምስክር በመሆን ለኢየሱስ ለመኖር ፈልግ።

**አስታውስ: እግዚአብሔር ቤተሰቦችህን፣ጓደኞችህን፣ጎረቤቶችህን፣እና በየቀኑ የምታገኛቸውን ሰዎች በመርዳት እና ቃሉን በማካፈል የሱን ዓላማ እንድተፈጽም ይፈልጋል።**

3. ከሌሎች ጋር ስለ እግዚአብሔር የምትነጋገርበትን መንገድ ተማር።በራሪ ወረቀቶች፣ቅዱሳን መጽሐፍት፣በየዕለት ህይወትህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት የሚተርክ መጽሐፍ፣እንዲሁም የኢየሱስ ታሪኮች ጥቂት መንገዶች ናቸው።

ለ. እግዚአብሔር እንድትሰራው የሚፈልገውን ነገሮች በልብህ እና በአዕምሮህ አትመው።
1. እግዚአብሔር ሌሎችን እንዴት በወንጌል መድረስ ትችል ዘንድ እንዲያሳይህ ከልብህ ጸልይ።
2. ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች የማካፈል እድሉን እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን ጠይቅ።
3. እንደ በራሪ ወረቀቶች፣መጽሐፍቅዱሶች እና ሌሎችም አጋዥ መርጃ መሳሪያዎች እንዲኖሩህ ሞክር።
4. በመልካም ሁኔታ ለመልበስ ሞክር።

ሐ. እግዚአብሔር በሰጠህ እድሎች ሁሉ ስለ ኢየሱስ ለመናገር ሞክር።
1. የእሱን እቅድ ትፈጽም ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ።
2. እግዚአብሔር በልብህ ያስቀመጠውን ነገር ለመፈጸም ታማኝ ሁን።

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. እግዚአብሔር እያወቅህ ለማደግ እና የእሱን ዓላማ በህይወትህ ለመፈጸም ተሰጥተሀልን?

አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, ከዛሬ ጀምሮ ራስህን ለእግዚአብሔር አስገዛ።

2. እግዚአብሔር እሱ የሚወደው ወይም የሚወዳት ሰው እንዲያደርግህ ጊዜህን በየቀኑ በጸሎት በመስቀሉ ስር ሆነህ ታሳልፋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, ዛሬ ጀምር።

3. ውጤታማ በሆነ መንገድ ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ትናገር ዘንድ ለመማር ፈቃደኛ ነህን?
አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, ዛሬ ወስን።

**ተግባራዊ ስራ**: በተጨማሪ መግለጫ ሐ ውስጥ የተጠቀሰውን የለውጥ ጸሎት በማጥናት እግዚአብሔር እንድትሆን የሚፈልገው አይነት ሰው ለመሆን ተዘጋጅ።
በተጨማሪ መግለጫ ሀ ላይ ያለውን በመጠቀም መንፈሳዊ ጉዞን ቀጥልበት፤አድርገኸው የማታውቅ ደግሞ ከሆነ ጀምር።

# ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መናገር
# ትምህርት 2
# ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች ስለመንገር የሚያስተምሩ የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል**፤ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

### ሀ. የጸሎት መርሆች

1. ችግሮች ሲገጥሙን ምን ማድረግ አለብን (ሉቃ 18:1)?
2. መጸለይ ያለብን ለማን ነው (1 ጢሞ 2:1-4)?
3. የሚረዱንን ሰዎች እንዴት እናገኛለን (ማቴ 9:36-38)?
4. ድፍረት እንዴት እናገኛለን (ሐዋ 4:31)?

### ለ. የኃይል መርሆች

1. የኃይል ምንጫችን ማን ነው (ሐዋ 1:8)?
2. ለመልዕክታችን ኃይል የሚሰጠው ማን ነው (1 ቆሮ 1:18)
3. የእግዚአብሔርን ኃይል ለሌሎች የሚያሳየው ምንድ ነው (1 ቆሮ 2:1-5)?
4. የመልዕክታችን ኃይል ሊሰራ የሚችለው ምንድ ነው (ዕብ 4:12)?

### ሐ. የመዝራት እና የማጨድ መርዎች

1. ስንመሰክር አመለካከታችን ምን መሆን አለበት (መዝ 126:5-6)?
2. የምንዘራው መጠን እንዴት ወጤቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል (2 ቆሮ 9:6)?
3. ምን አይነት መዝራትን ነው ማድረግ ያለብን (ገላ 6:7-10)?
4. ምን መዝራት አለብን, የት መዝራት አለብን, ውጤቱን የሚወስነው ምንድ ነው (ሉቃ 8:5-8, 11-15)?

**መ. የአቀራረብ መርሆች**

1. ኢየሱስ በዮሐ 4:5-42 ምን አይነት መርሆችን አሳየን?
2. ወንጌልን ስናካፍል ሁለቱ አቀራቦች ምንድ ናቸው (ይሁዳ 22 - 23)?
3. ወንጌልን ስናካፍል ማድረግ የሌለብን ምንድ ነው (2 ቆሮ 4:1-6)?
4. ወንጌልን ስናካፍል ማስወገድ ያለብን ምንድ ነው (ቲቶ 3:4-9)?

**ሠ. የውጤት መርሆች**

1. የሰዎችን ንስሐ ይቅር የሚለው ማን ነው (2 ጢሞ 2:24-26)?
2. ወንጌልን ስንሰብክ የእግዚአብሔር ቃል የሚፈጽመው ምንድ ነው (ኢሳ 55:10-11)?

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: *በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።*

*የትኞቹን መርሆች ነው በህይወትዎ መጨመር የሚያስፈልግዎ፤ለመጨመር ምን ማድረግ አለብህ?*
*ተግባራዊ ስራ: ሁሉንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የወንጌል ስብከት መርሆች በህይወትህ ላይ ለመጨመር ፈልግ።*

# ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች መናገር
# ትምህርት 3
# የምናካፍለው መልዕክት

የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፤አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).

**ለምናካፍለው መልዕክት መግቢያ**: ብዙ ጊዜ በግማሽ ልብ ሆነን ቃሉን ግማሽ ልብ ከሆነ ውጤት ጋር እናካፍላለን (ይህን ጸሎት ጸልይ ከዛም ወደ ሰማይ ትሄዳለህ) ።በእውነት ዓለምን መቀየር የምንፈልግ ከሆነ ቃሉን ልክ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ፤ጴጥሮስ እና ጳውሎስ መስበክ አለብን። በእግዚአብሔር ፊት ስለሚደረግ ንስሀ እና በኢየሱስ ላይ ስላለ እምነት (ሐዋ 20:21) የሚያስተምረው ይህ ርዕሰ ጉዳይ ይህንን ልታደርጉ የሚያስችላችሁ መሳሪያ ነው።ቃሉን ለማካፈል በመጀመሪያ የሚለውን በሚገባ መረዳት አለብን።መልዕክቱ አራት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት:

1. የሰው ትልቁ ችግር ሐጢያት ነው። (ኢሳ 53:6, ሮሜ 3:23)
2. ይህ ሐጢያት ከእግዚአብሔር ለይቶናል። (ኢሳ 59:2, ሮሜ 6:23)
3. እግዚአብሔር የዘለዓለም ህይወትን እናገኝ ዘንድ አንድያ ልጁን በእኛ ሐጢያት ምትክ ለዓለም በመስጠት ፍቅሩን አሳይቶናል። (1 ጴጥ 3:18, ሮሜ 5:8)

**ማስታወሻ: የዘለዓለም ህይወት ማለት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ዘለዓለማዊ ወዳጅነት ነው (ዮሐ 17:3)**

4. የዘለዓለም ህይወትን ለማግኘት ህይወታችንን ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን (ሉቃ 14:26, 27 & 33, ሮሜ 10:9-13)

**ወንጌልን የመስበክ ዓላማ**: ወንጌልን የመስበክ ዓላማ አንድ ሰው የዘለዓለም ህይወትን እንዲያገኝ ነው፤እንጂ ወደ ሰማይ ቤት ለማገባት አይደለም።በዮሐ 17:3 "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"ይላል።
ሰዎች በህይወታቸው ያለባቸውን ችግሮችን ሁልጊዜ መፍታት ይፈልጋሉ።በምታገኛቸው ጊዜ እነሱ በህይወታቸው የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት እርዳታን ይፈልጋሉ።በሙሉ ልብ ኢየሱስን መከተል ብቸኛው የህይወት ችግሮች መፍትሔ መንገድ ነው።
አንድ ሰው የዘለዓለም ሕይወትን ያገኝ ዘንድ ሦስት ነገሮች መሆን ይገባቸዋል። ንስሀመግባት፤መቀበል፤እና እንደገና ማቀድ ያስፈልጋቸዋል።ንስሀ መግባት ያለባቸው ወደ እግዚአብሔር ነው።እነሱ ሐጢያታቸው በእውነት የእግዚአብሔርን ልብ እንዳሳዘነ በማወቅ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው፤በእነሱ፤በቤተሰቦቻቸው፤ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ ስለሆነ አይደለም።ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው እና ጌታቸው አድርገው መቀበል አለባቸው።ይህ ሙሉ በሙሉ ህይወታቸውን (የጋብቻ ህይወታቸውን፤ግባቸውን፤ምኞታቸውን እና ርስታቸውን ያጠቃልላል) ለእግዚአብሔር ማገዛት ነው።(ሉቃ 14:26-27 & 33); ኢየሱስ የዓለምን ሐጢያት ለማንጻት በመስቀል ላይ የሰራውን የመዳን ሥራ መታመን (ዕብ 9:14); እንዲሁም ለሚያገኑት ለማኛውም ሰው ኢየሱስ አዳኝና ጌታቸው መሆኑን መናገር።(ሮሜ 10:9-10). አንድ ሰው በእውነት ንስሀ ከገባ እና ኢየሱስን እንደግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖር እንደገና ያቅዳል። (ዮሐ 14:21-23, 1ዮሐ 5:1-3).
የሚቀጥለው ገጽ እንዴት ስለ እግዚአብሔር ለሰዎች መንገር ላይ ያተኮረ ጠቃሚ አርዕስተ ጉዳይን ይዟል።ስለ ኢየሱስ ለመናገር የሚስፈልግህን እውቀት ይሰጥሃል።ያገኘኸው እውቀት ውጤታማ ሆኖ የሚሰራው ጊዜህን በአግባቡ ተጠቅመህ በጸሎት ስታሳልፍ ብቻ ነው።

**ግብ:** ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር የመናገር ግቡ በቀላሉ እና በግልጽ እግዚአብሔር ለእነሱ ያደረገላቸውን ነገር መናገር ነው፤መንፈስ ቅዱስም ሰውዬው ህይወቱን ለእግዚአብሔር ይሰጥ ዘንድ ያደረግዋል፤ (መንፈሳዊ ልደት). ሮሜ 10:14-17, ዮሐ 6:44; 3:3, 5-6

**ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር ለመናገር የተሰጡ ደረጃዎች**
ደረጃ. 1. በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንደቀረብክ እርግጠኛ ሁን፤
ያልተናዘዝከው ሐጢያት በአንተና በእግዚአብሔር መሐከል መኖር የለበትም።ለሚጠፉት ነፍሳት ከእውነተኛ ከልብ የፈለቀ ፍቅር ተነስተህ እንጂ ሐይማኖታዊ ስርዓትን ለመፈጸም ብቻ ወንጌልን እየሰበክህ እንዳልሆነ እርግጠኛ ሁን።መዝ 126:5-6

**ደረጃ. 2 ውይይታችሁን በጥያቄ ወይም ምሳሌ ክፈት**
ዘና በል።ሰዎች እራሳቸውን በሚገባ እንዲገልጹ ፍቀድ።ይህ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚነገረውን መልዕክት በአግባቡ እንዲሰሙ ልባቸውን ይከፍታል።ጥያቄ ወይም ምሳሌው ግልጽ እና የሚያውቁትን ባህል ወይም ማህበረሰባዊ ነገሮችን ያቀፈ ሆኖ የመስማት ፍላጎትን የሚቀሰቅስ መሆን ይኖርበታል።

ምሳሌ 1: በዮሐ 4 ላይ የኢየሱስ እና ሴቲቱ በውሀ መቅጃው ስፍራ የሆነው ታሪክ መልካም ምሳሌ ነው። "ውሐ አጠጪኝ" እንዲሁም "የህይወት ውኃ አለኝ"

ምሳሌ 2: በህንድ ብዙ ጊዜ እንዲህ እያልን እንጠይቃለን፤"ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ አግኝተኃልን/አግኝተሻልን?"የህንድ ሐይማኖት የእግዚአብሔርን መንገድ በማግኘት ላይ ያተኩራል። ግልጽ የሆነው የምስክርነት ቃል እግዚአብሔር ለአንተ የሰራው ስራ ላይ ያተኩራል ወይም አንድ አንተ የምታውቀው ተመሳሳይ ችግር ያለበት ሰው እንደ አድማጭ ሊጠቀምበት ይችላል።
ለምሳሌ: ስለፈውስ የምትናገው ምስክርነት በተመሳሳይ በሽታ ያለበትን ሰው የመስማት ፍላጎት ሊያነሳሳው ይችላል።

**ደረጃ. 3. ለሰዎች እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ነገር ንገራቸው**

***ሀ. ሐጢያት*** (ሮሜ 3:23)
ጥያቄ: ሐጢያተኛ እንደሆንክ ታውቃለህን?
መልስ: አንድ ሐጢያት ብቻ ሐጢያተኛ ሊያደርጋቸው እንደሚችል አስረዳቸው፡፡እንዲሁም ለእግዚአብሔር ከመኖር ውጪ ያለው ሁሉ ሐጢያት እንደሆነ አስብ፡፡እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው እና ለእነሱ መልካም የሆነውን ሁሉ እንደሚያስብ ያለማመናቸው ወይም ያለመረዳታቸው ምልክት ነው፡፡
1 ዮሐ 3:4; 1:8-9, ምሳ 2:4, ሮሜ 14:23b
ምሳሌ: በብርጭቆ ውስጥ ያለ የአፕል ጁስ; የአንድ የተመረዘ ጠብታ የማይጠጣ ያደርገዋል፡፡

***ለ. መለየት*** (ሮሜ 6:23)
ጥያቄ: የሐጢያት ውጤት ምን እንደሆነ ታውቃለህን?
መልስ: መልሳቸው ምንም ቢሆን ሐጢያታቸው ከእግዚአብሔር እንደለያቸው፤ህይወታቸውን፤ቤተሰባቸውን፤ጓደኞቻቸውን፤ማህበረሰባቸውን እንዳበላሸው እና በይበልጥ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ዘለዓለማዊ መለየት፤ሞት እና ሲኦልን እንዳመጣባቸው እንዲረዱ እርዳቸው፡፡ ሐጢያት የችግሮቻቸው ምክንያት እና ለወደፊትም ምክንያት እንደሚሆን ንገራቸው፡፡
ምሳ 8:36; 14:11; መዝ 9:17; ያዕ 1:13-16
ምሳሌ: መኪና ጎታች ትራክተር በሰንሰለት መኪናን ወደ ፊክታ ስፍራ በሚጎትትበት ጊዜ፤ለመሰበር የአንድ ሰንሰለት መገናኛ መቀንጠስ በቂ ነው፡፡

***ሐ. ምትክ*** (ሮሜ 5:8)
ጥያቄ: እግዚአብሔር ሐጢያትህን ሊያስወግድ ምን እንደሰራ ታውቃለህን?
መልስ: መልሳቸው ምንም ቢሆን፤እግዚአብሔርን(ኢየሱስ) እንዲረዱ እና ስለሚወዳቸው ለእነሱ ሐጢያት ሲል እንደሞተላቸው እንዲያውቁ እርዳቸው፡፡
መልካም የሆነ ጊዜ እስኪያገኙ ሊጠብቃቸው አይፈልግም፡፡እሱ ሐጢያት ለጊዜው አስደሳች እንደሆነ ያውቃል፤ነገር ግን መጨረሻው ሞት ነው ምክንያቱም መለኮታዊውን ህግጋት እየተጻረረ ነውና (የእግዚአብሔር የግብረገብ ህግ እጅግ መልካም ነው ምክያቱም አሱ አዋቂ ነውና).እሱ የዘለዓለም ህይወት (እውነተኛ ሰላም፤ደስታ እና ሀሴት) እንደሚሰጣቸው ንገራቸው፡፡እሱ በልባቸው ሊኖር እና ሐጢያትን እንዲያሸንፉ ሊረዳቸው ይችላል፡፡እሱ አንድያ ልጁን ወደ ምድር ልኮ እና ለሐጢያታችን በመስቀል ላይ እንዲሞት ወስኖበት እና የሐጢያታቸውን ቅጣት ከፍሎ ፍቅሩን እንዳሳየን ንገራቸው፡፡የእነሱ መልካምነት ወይም ሐይማኖት ሐጢያታቸውን ሊያስወግድ እንደማይችል አሳውቃቸው ምክንያቱም ያ ቆሻሻን በቆሻሻ ለማጽዳት እንደመሞከር ነውና፡፡
ዮሐ 3:16, 1 ዮሐ 3:8, ሮሜ 6:5-6
ምሳሌ: ሞት የተፈረደባቸው እስረኞች; የወንጀላቸውን ዋጋ የሚከፍሉ ከሆነ፤ይሞታሉ፡፡አንድ ሰው በነሱ ምትክ የሚሞትላቸው ከሆነ ግን ነጻ ይሆናሉ፡፡

***መ. መማርክ:***
ጥያቄ: እንዴት ሐጢያትህ እንደሚነጻ እና እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የዘለዓለም ህይወት እንደምትቀበል ታውቃለህን?
መልስ: አንድ ሰው ወደ ዘለዓለም ህይወት እንዲገባ ሦስት ነገሮች መሟላት አለባቸው፡፡ንስሀ መግባት፤መቀበል እና እንደገና ማቀድ አለባቸው፡፡

(1). ንስሀ መግባት (ሮሜ 2:4)

መልስ: ንስሀ የምንገባው ወደ እግዚአብሔር ነው።ሐጢያታቸው የእግዚአብሔርን ልብ ስላሳዘነ ማዘን አለባቸው፤እንጂ ለነሱ፤ለቤተሰቦቻቸው እና ለጓደኞቻቸው በተደረገላቸው ነገር አይደለም።ከሐጢያታቸው ተመልሰው ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ለመኖር መሻት ይኖርባቸዋል።
ምሳሌ: በመንገድ ስትራመድ;አደገኛ ነገር ፊትህ ላይ ካየህ አቅጣጫህን ቀይረህ በሌላ መንገድ ተጓዝ።
(2). መቀበል (ሮሜ 10:9-13)
መልስ: እነሱ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታቸው እና አዳኛቸው አድርገው መቀበል አለባቸው።ይህ በአጠቃላይ ህይወታቸውን (የትዳር ግንኙነታቸውን፤ግባቸውን፤መሻታቸውን እና እርሳታቸውን) ለእግዚአብሔር ማስረከብ ነው (ሉቃ 14:26-27 እና 33), እንዲሁም በኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ በመታመን ሐጢያታቸውን ለማስወገድ እና ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ኃይልን ይሰጣቸዋል።ኢየሱስ አዳኛቸው እና ጌታቸው እንደሆነ ለሚያገኙት ለማንኛውም ሠው መናገር አለባቸው። (1 ዮሐ 1:9, ዕብ 9:14)
ምሳሌ: አንድ ሰው ለስራው የሚሆን የስራ አስተዳዳሪ ሾመ ምክንያቱም ያ ሰው እሱ በስልጠና ዋጋውን እንደከፈለ እና ከእሱም ይልቅ ለስራው የተሻለ ሰው እንደሆነ ያውቃል።እሱም ስለ አስተዳዳሪው ለሌሎች ሲናገር አያፍርም።
(3). እንደገና ማቀድ (ሮሜ 6:17-18)
መልስ: በሙሉ ልባችን በክርስቶስ በምንታመንበት ጊዜ በህይወታችን እግዚአብሔርን በመታዘዝ ለመኖር እንደገና በማቀድ እንወስናለን ምክንያቱም እሱ ለእኛ የተሻለውን ያስባልና።
ምሳሌ: ለትራፊክ ፖሊስ የምንታዘዘው የሚያስተላፉት መልዕክት እና ህግጋታቸው ለራሳችን ጥቅም ስለሆነ ነው።

**ሠ. ማጠቃለያ**
ጥያቄ: ልብህን እና ህይወትህን ለኢየሱስ ለማስገዛት ፈቃደኛ ነህን?
መልስ: ይህ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የወንጌል ስብከት ክፍል ነው።የሰው ልጅ ነፍስ ዘለዓለማዊ እጣ ፈንታ በሚዛን ይመዘናል።እራሳቸውን ለጌታ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ፤በጥንቃቄ ወደ ወንጌል ስብከት ይሂዱ። "ገባችሁ (ያልገባቸውን በመጥቀስ)? "ብላችሁ ጠይቁ።ሙሉ በሙሉ ወንጌል ምን እንደሆነ ከተረዱ በኂላ የማጠቃለያውን ጥያቄ ጠይቃቸው።
ህይወታቸውን ለክርስቶስ ለመስጠት ፈቃደኛ የሚሆኑ የማይመስሉ ከሆነ፤በጥንቃቄና በፍቅር እግዚአብሔርን አለመታዘዝ አደገኛ ነገር እንደሆነ አስረዳቸው።

1 እንዲህ ብለህ አስረዳቸው:
(1.) እግዚአብሔር በመንፈሱ ወደ እራሱ ካመጣው በስተቀር ማንም በፈለገ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መምጣት አይችልም። ዮሐ 6:44
(2.) እሱ/እሷ ለነገ ቀጠሮ መያዝ አይችሉም።እነሱ አሁን የሚሞቱ ከሆነ የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ፍርድ ያገኛቸዋል።2 ቆሮ 6:2
(3.) እነሱ ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ከሆነ፤እጅግ በጣም አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል።ምሳ 29:1
የሚወስኑት ውሳኔ አስፈላጊነት ግልጽ ሆኖ ከተረዳህ በኂላ፤አንድ የማጠቃለያ ጥያቄ ጠይቃቸው።በድጋሚ አይሆንም ካሉ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ንገራቸው፤አንተም እንደምትወዳቸው እና እንደምትጸልይላቸው ንገራቸው።አሁን ስለሚያውቁት እውቀት ተጠያቂ እንደሆኑ አሳስባቸው።
አንድ ሰው ራሱን ለኢየሱስ ክርስቶስ ለመስጠት መዘጋጀቱን ስታውቅ፤እንደምትጸልይለት ንገረው፤በሐጢያቱ እንዳዘነ ድምጹን ጮክ አድርጎ መናዘዝ እና ለመለወጥ መፈለግ ይገባዋል።ህይወታቸውን ሁሉ ለክርስቶስ ማስገዛት እንዳለባቸው ንገራቸው።ለእሱ እንደሚገባ ይመላለሱ ዘንድ ኢየሱስ ወደ ልባቸው ገብቶ ህይወታቸውን በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላው እንዲጸልዩ ንገራቸው።ጸሎታቸውን እግዚአብሔር በማመስገን በኢየሱስ ስም እንዲያጠናቅቁ አስተምራቸው።

የመጨረሻ ጥያቄ: ኢየሱስ ለአንተ ማን ነው?
መልስ: የኔ ጌታ እና አዳኝ ነው።ሌላ መልስ ከተመለሰ፣ምን ማለታቸው እንደሆነ ጠይቅ፤ያልገባቸውን ነገር እንደገና አብራራላቸው።
ደረጃ 4. ***እግዚአብሔር በማወቅ ማደግ እንዲጀምሩ እርዳቸው***
አንድ ታታሪ ገበሬ በአግባቡ ሳይሰበስብ እና ሳይበሰብስ እንዲሁም ተገቢውን ሥራ ሳይሰራ ፍሬ ለመልቀም ወደ መስክ መውጣት አይገባውም፤ምንም የሚሰበሰብ ፍሬ አያገኝምና፤ቤተክርስቲያን ወይም ማህበረሰቡ አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ለመምራት ተገቢውን መሰጠት እና ሥራ መስራታቸውን እርግጠኛ ሳይሆኑ መጠበቅ ተገቢ አይደለም።

የሚከተሉትን በጥንቃቄ እና በፍቅር ህይወቱን ለክርስቶስ ለሰጠ አንድ ሰው አስረዳ
**ሀ.** ለህይወት እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብለሃል።ይህን መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ውልደት ወይም ከመንፈስ መወለድ ይለዋል።ዮሐ 3:3, 5-6

**ለ.** አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እንዲሁም ለእሱ ለመኖር ኃይል አለህ። (ዮሐ 1:12-13, ሮሜ 8:15-17) ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ይኖራል።እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላህ ፈቀድለት።በህይወትህ የሱን ዓላማ ትፈጽም እና ለእግዚአብሔር ትኖር ዘንድ ኃይል ይሰጥሃል።ከጠየቅነው በመንፈሱ ሊሞላን ቃል ገብቶልናል። (በመንፈስ ቅዱስ ይሞሉ ዘንድ ምራቸው) ሐዋ 2:4; 4:31, ሉቃ 11:13

**ሐ.** እግዚአብሔር በህይወትህ የሱን ዓላማ እንድትፈጽም ከዘለዓለም ሞት አድኖሀል።ሰውነትህ እንዲያድግ እና በጤንነት እንዲኖር የተመጣጠነ ምግብ እንደሚያስፈልግህ ሁሉ እግዚአብሔርን በማወቅ ታድግ እና በህይወትህ የሱን ዓላማ ትፈጽም ዘንድ መንፈሳዊ ህይወትህ እንዲያድግ መንፈሳዊ ምግብ በየዕለቱ መመገብ ይኖርብሀል።ይህ መንፈሳዊ ምግብ በየዕለቱ ልታነበውና ልትኖረው የሚገባህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው።ሉቃ 4:4, ሮሜ 6:17-18, 2 ጢሞ 1:9

**መ.** እንደ ልጅ ስታድግ እና ስትማር መውደቅ እና መደናቀፍ ይኖራል፤በመንፈሳዊ ነገር ለማደግ በምታደርገው ሂደት ልትታገል ይገባል።ተስፋ አትቁረጥ።ሐጢያትህን መናዘዝ፤እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መፈለግን አትርሳ፤በመንፈሳዊ ህይወትህም ታድጋለህ።እግዚአብሔርም ይረዳሃል።
1 ዮሐ 1:9; 2:1, 114, ዮሐ 16:13; 14:26-27, ኤፌ 3:16

**ሠ.** ምክንያቱም አንተ ሰው ነህ (ስጋ ደካማ ነው), ለክርስቶስ ያለህን መሰጠት ማደስ እና በጸሎት በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይኖርብሃል፤ከዛም ፈቃዱን ለማድረግ ከመፈለግ ይልቅ ማድረግ ትጀምራለህ።ሉቃ 9:23, ዮሐ 15:7, 23-24, ገላ 5:16 & 25, ሐዋ 4:31, ኤፌ 5:18

**ረ.** ክርስቶስ ያደረገልህን ነገር ለሌሎች ለመመስከር እና እሱ የህይወትህ ጌታ እና አዳኝ እንደሆነ ለመናገር ፈቃደኛ ሁን።ያ እምነትህን ያሳድገዋል እግዚአብሔርም ደግሞ ይባርክሃል።
ሐዋ 1:8, ማቴ 10:32-33, ሉቃ 12:8-9, ያዕ 5:20, መዝ 126:5-6

**ሰ.** የውኃ ጥምቀት በመውሰድ የአንዲት ወንጌላውያን አጥቢያ ቤተክርስቲያን ህብረት አባል መሆን ይኖርብሀል።ይህ ከሐጢያት ዘወር ማለትህን እና በክርስቶስ አዲስ ሰው መሆንህን በህዝብ ዘንድ የሚያሳይ ምስክርነት ነው።በመንፈሳዊ ህይወታቸው ጠንካሮች ከሆኑ ወገኖች ጋር ጠንካራ ህብረት ሊኖርህ ይገባል።ሐዋ 2:38-39, ሮሜ 6, ዕብ 10:24-25

**ክትትል**
እራሳቸውን ለክርስቶስ እንደሰጡ እና በየዕለት ኑሯቸው እንዴት ለክርስቶስ መኖር እንዳለባቸው እንዳወቁ እርግጠኛ ከሆንህ በኋላ በቀጣይ ልታገኛቸው ትችል ዘንድ አድራሻቸውን ተቀበል፤ለምሳሌ ስም፤አድራሻ፤ስልክ ቁጥር፤እና የኢሜይል አድራሻ።ጸልይላቸው እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ወይም

አዲስ ኪዳን እንኳን እንዳላቸው እርግጠኛ ሁን፡፡የሚቻል ከሆነ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔርን በማወቅ ያድጉ ዘንድ እርዳቸው፡፡አንተ እግዚአብሔርን በማወቅ ያድጉ ዘንድ ለመርዳት የማትችል ከሆነ ለሌላ ለሚችል ሰው አስተላልፋቸው፡፡በግል ልታገኛቸው የማትችል ከሆነ ለተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጠና የርቀት ትምህርት ወይም የኢንተርኔት የቀጥታ ስልጠና እንዲወስዱ መርዳት መልካም ነው፡፡የአንዲት ወንጌላውያን አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል እስኪሆኑ ድረስ በስልክ፤በኢሜይል፤ወይም በፖስታ (የሚቻል ከሆነ ቢያንስ በየሳምንቱ) አግኛቸው፡፡

**ችግሮችን መፍታት**

ሀ.እነሱ "በኢየሱስ አምናው" ይላሉ( ነገር ግን በግልጽ ምኞቶቻቸውን ይፈጽማሉ).

<u>መልስ:</u> በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡ (ማቴ 7:21) በእውነት ከልብህ ለኢየሱስ ተሰጥተሀልን ወይስ ዝም ብለህ መንግስተ ሰማይ እንዲያስገባህ ብቻ ነው ስሙን የምትጠራው?

ለ. እግዚአብሔር ማንንም ወደ ሲኦል አያስገባም

<u>መልስ:</u> እንዲህ በማለት ጀምር፤ "እጅግ በጣም ጥሩ ጥያቄ ስላስነሳ በጣም ደስተኛ ነኝ፤እንዴት እናውቃለን? እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል እንዴት እናውቃለን? ሁለት ልናውቅበት የምንችልበት መንገድ አለ:

(1) አንዱ የሰው የአዕምሮ ምርምር፡፡ ቁጭ ብለን ስለ እግዚአብሔር እያሰላሰልን ወደ አንድ መደምደሚያ እንድረስ፡፡ይህ አቀራረብ ሰዎችን እንግዳ ወደሆነ ሐይማኖታዊ አስተሳሰብ መርቷቸዋል፡፡ ሌላው

(2), ራዕይ/መገለጥ ነው፡፡እግዚአብሔር ራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ እና በአንድያ ልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ገልጦታል፡፡ጥያቄው ሌላው ሰው የሚያስበው አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ እና በልጁ በኢየሱስ በኩል የተናገረው ነው፡፡

ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን አላምንም

<u>መልስ:</u> አንዳንድ ሰው እንዲህ ሊል ይችላል. "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን አላምንም፤ በሌላ መንገድ ልታሳምነኝ ይገባል." በመሰረቱ መጽሐፍ ቅዱስን እናስተምራለን እንጂ ለመጽሐፍ ቅዱስ መከላከል አንችልም፡፡ ይህንን ተቃውሞ በሚከተለው መንገድ እናየዋለን: "መጽሐፍ ቅዱስን አታምንም (የሚሰማችሁን ሰው ስሙን በመጥራት) ? ያ አስደሳች እና በእርግጥ መልካም አጋጣሚህ ነው፤ነገር ግን ጥያቄ ልጠይቅህ እወዳለሁ፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ሰው እንዴት የዘለዓለም ሕይወትን እንደሚያገኝ እና ወደ መንግስተ ሰማይ እንደሚገባ ሲያስተምር የምትረዳው ምንድ ነው (98% ጊዜ ወርቃማውን ህግጋትን በመጠበቅ ወይም የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል ነው ብለው ይመልሳሉ)?

"እኔ ለዛ ነበር የፈራሁት (የሚሰማችሁን ሰው ስሙን በመጥራት) ፤አንተ ዋናውን የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት ባለመረዳት ውድቅ አድርገኸዋል ብለህ ልትመልስ ትችላለህ፡፡

መ. እኔ በእግዚአብሔር አላምንም

<u>መልስ:</u> ለምን አታምንም? (ዋናው ሰዎች በእግዚአብሔር የማያምኑበት ምክንያት የለመዱትን ሐጢያት መተው ስለማይፈልጉ ወይም እራቸውን እግዚአብሔር እንደማይወዳቸው ስለሚያሳምኑ እና ለራሳቸው የተሻለውን ስለሚመኙ ነው፤መልሳቸው ችግራቸው ምን እንደሆነ ያሳያል) ኦ፣ገባኝ፤የአንተ ችግር ከተለማመድከው ሐጢያት መመለስ ስለማትፈልግ ነው ወይም እግዚአብሔር እንደሚወድህ ስለማታምን ነው፡፡

***ማጠቃለያ*:** እዚህ የቀረቡልህ ጽሁፎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር እንድትናገር የሚያስችሉህ መሳሪያዎች ናቸው።መጽሐፍ ቅዱስን አሰላስል፤የሚቻል ከሆነ፤ጌታን ለማያውቅ ሰው ከመስጠህ በፊት ከሌላ ከምታውቀው የኢየሱስ አማኝ ጋር አብረህ ሂድ።በጽሁፎቹ የተጠቀምከውን ያህል በይበልጥ የአንተ የህይወትህ አካል ይሆናሉ፤የምትሰራውን ሁሉ ከልብህም ማድረግ ትችላለህ። የተወሰኑ ባህላዊ ስፍራዎች ስትሄድ የተለየ ስልጠና እንደሚያስፈልግህ አትዘንጋ።

*መረጃዎቹ ከታች ከተጠቀሰው አድራሻ ይገኛሉ:*
U.S. Center for World Missions, 1605 Elizabeth Street, Pasadena, CA. 91104
**www.uscwm.org**
MAY GOD BLESS YOU AS YOU SHARE THE GOSPEL WITH OTHERS?
Some of the above material on Handling Problems is based on material from "Evangelism Explosion" by Dr. James Kennedy.

***መሠረታዊ ጥያቄዎች*:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

*ውጤታማ መሆን ትችል ዘንድ የምንሰጥህን መልዕክት ለማጥናት ፈቃደኛ ነህን?*
*ተግባራዊ ሥራ:* ከቤተሰብ አባላት ወይም ከጓደኛዎ ጋር የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈልን ተለማመድ።

# ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መናገር
# ትምህርት 4
# የአንተ ግላዊ ታሪክ

ከታች የተጠቀሱትን ርዕሰጉዳይ በመጠቀም በዝርዝር የራስህን ግላዊ ታሪክ ጻፍ

1. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ከመቀበሌ በፊት የነበረኝ ህይወት:

2. ክርስቶስ እንደሚያስፈልገኝ እንዴት ተረዳሁ:

3. የኢየሱስ ተከታይ እንዴት ሆንኩኝ:

4. ኢየሱስ ህይወቴን እንዴት ትርጉም ያለው አደረገው:
5. እግዚአብሔር በግልህ የሚያስፈልጉህን (ፈውስ፤የገንዘብ በረከት እና ሌሎችም ነገሮች) ያሟላልህን ነገሮች ዘርዝር።

# ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መናገር
# ትምህርት 5
# ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች ለመናገር
# ልታደረጋቸው የምትችላቸው ነገሮች

የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፤አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).
ቆላ 3:17 የምትናገረውን ወይም የምትሰራውን ማንኛውንም ነገር የኢየሱስ ክርስቶስ ወኪል እንደሆንህ አድርገህ አድርገው።በእሱ በኩል ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርብ።

***ሀ. ቃላትን በመጠቀም ለሰዎች ወንጌልን መስበክ***

1. <u>ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር በማስተማር</u> እንዴት እናካፍላለን።
ሀ. ስለ እግዚአብሔር ስትናገር ትሁት ግን ደፋር ሁን።
ለ. ፊት ለፊት ወይም በስልክ ማስተማር ትችላለህ
ሐ. የየዕለት እንቅስቃሴያችን ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር ለመናገር እድሎችን ይሰጠናል።
መ. ስለምታውቃቸው ስለ እግዚአብሔር መስማት ስላለባቸው ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ለመናገር እግዚአብሔርን ጠይቅ፤የምትሰብክበትን ትክክለኛ ጊዜ ለመወሰን ጸልይ።
ሰ.እግዚአብሔር ስለ እሱ ሊያውቅ የሚፈልግን አንድ ሰውን ወደ አንተ ሲያመጣ ለመለኮታዊ ቀጠሮ ዝግጁ ሁን።እነሱ በሚጠይቁት ጥያቄ ወይም በሚያነሱት ሀሳብ ልትናገር ትችላለህ።

2. <u>በተጻፉ ጽሁፎች</u> እንዴት ስለ እግዚአብሔር ልትናገር ትችላለህ፤

ሀ. በራሪ ወረቀቶችን ለሰዎች ማደል ትችላለህ።ሁልጊዜ በራሪ ወረቀቶችን ያዝ፤ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚናገሩ ወረቀቶች፤እና ስለ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ችግሮች የሚናገሩ ጽሁፎች ለምሳሌ ስለ አደንዛዥ ዕጽ፤ድብርት፤እና ሌሎች የህይወት ጉዳዮች የሚያስተምሩ ጽሁፎችን ያዝ።በምትችልበት ጊዜ ሁሉ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ስጣቸው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ፤አዲስ ኪዳን ወይም ሌሎች ለብቻቸው የታተሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መስጠት ትችላለህ።ይህንን ልናደርግ የምንችልበት አንዱ መንገድ ልዩ በሁኑ ባህላት ለምሳሌ የገና በዓል፤የልደት በዓል፤ወይም ወደ ክልላችሁ አዲስ ለመጡ ወገኖች የእንኳን ደህና መጡ ባዕል ላይ ሊሆን ይችላል።
ሐ. መደበኛ በሆነ የፖስታ የኢሜይል አድራሻ በመጠቀም ደብዳቤ፤በራሪ ወረቀቶችን ወይም የመጽሐፍ ክፍሎችን ለምትጽልዩላቸው ወገኖች መላክ ትችላላችሁ።

3. <u>መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተምሩ የድምጽ እና የምስል (የቪዲዮ) ቅጂዎችን</u> እንደ ስጦታ አድርጋችሁ መላክ ትችላላችሁ። የእግዚአብሔር ቃል ኃይለኛ የጦረር መሳሪያ መሆኑን አስታውስ።በሰዎች ልብ እና አዕምሮ ውስጥ የገቡ የሰይጣን ኃይላትን አስድወግዶ የእውነትን ወንጌል ያበራላቸዋል። (ዕብ 4:12 እና 2ቆሮ 10:4-5). በእግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳ እንደሚፈነዳ ቦምብ ነው።(ኢሳ 55:11). ለሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመናገር በብዙ መንገድ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

**ሰ. አንተ በምትሰራቸው ነገሮች ስለ እግዚአብሔር መናገር (የምህረት አገልግሎት)**

1. <u>ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር የመስጠት ባህልን</u> ማሳደግ ያስፈልግሀል።

2. <u>በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ በአካላዊ፣በቁሳዊ፣በአዕምሮ፣በውስጣዊ ስሜት፣እና በመንፈሳዊ ነገር የሚስፈልጋቸውን ሁሉ ለመርዳት</u> ልትሞክር ይገባል።ይህ ምን ያህል እንደምታስብላቸው ያሳያል፣ወንጌልም እንድትነግራቸው እድሎችን ይከፍትልሀል። (ማቴ 10:7-8, ዮሐ 6:5-11, 26-27, ሉቃ 6:17-18, ሐዋ 14:8-10)

3. መጀመሪያ <u>የምታውቃቸውን አማኞች፣ቤተሰቦችህን እና ስለ እግዚአብሔር የማያውቁ ሰዎችን ልትረዳ ይገባል</u>። (ዮሐ 13:35 እና ገላ 6:10).

4. ሰዎችን ልትረዳ በምትዘጋጅበት ጊዜ <u>የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መጠየቅ አለብህ</u>።

**ማስታወሻ:** ለሚያስፈልጋቸው ነገር ሁልጊዜ አንድ ነገር ማድረግ ትችላለህ።ምንም ከሌለ ከሰው ገር መጸለይ ትችላለህ።ሜርሲ(የምህረት) አገልግሎት ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በህብረት በመሆን ታላቅ የሆነ ለውጥ ለማምጣት ይሰራል።

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

ለምታውቃቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት ታካፍላለህ?

**ተግባራዊ ሥራ:** አንድ የተቸገረን ሰው የሚያስፈልገውን ነገር በመርዳት የእግዚአብሔርን ቃል ለማካፈል ሞክር።በምትረዳው ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል የምታካፍልበትን እድሎችን በመፍጠር እግዚአብሔር ያስተማረህን ንገራቸው።ስለሆነው ሁሉ ግልጽ የሆነ ታሪክ ጻፍ።

# ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መናገር
# ትምህርት 6
# በየዕለቱ ለምታገኛቸው ሰዎች ስለ እግዚአብሔር መናገር

የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፣አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).

**የሚከተሉት በየዕለቱ ለምታገኛው እና በማህበረሰብ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ለመናገር የምትችላቸው ጥቂት ነገሮች ናቸው።አንደኛ ሰዎችን መውደድ፣እና ጓደኛቸው ለመሆን መሞከር ነው፣ከዛም እግዚአብሔር የምታደርገውን ያሳይሀል።**(ምሳ 18:24 እና 16:29)

*<u>ለሰዎች በመጸለይ</u> የእግዚአብሔርን እውነት ተናገር*

*በጸሎት የእግዚአብሔርን እውነት መናገር ዋና ዓላማው ሰዎች የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲያዩ እና ፍቅሩን እና በተመለሰላቸው የጸሎት መልስ ርህራኤውን ይለማመዱ ዘንድ እንዲረዳቸው ነው።*
በጸሎት የእግዚአብሔርን እውነት የመናገር ዓላማ በተመለሰላቸው የጸሎት የእግዚአብሔርን ፍቅር በሚያሳየው የወንጌል መልዕክት ሰዎችን ለመድረስ ነው።

**በጸሎት የእግዚአብሔርን እውነት ልታካፍል የምትችልባቸው መንገዶች:**
1. በየዕለት እንቅስቃሴህ ለምታገኛቸው ሰዎች ለሚያስፈልጋቸው ነገሮች በመጸለይ።
2. የእግዚአብሔርን ፍቅር ልትነግራቸው ለምትፈልጋቸው ሰዎች ለመጸለይ እድሎችን በመፈለግ።
3. የእግዚአብሔርን እውነት ልታካፍላው የምትፈልጋቸውን ሰዎች በመጎብኘት እና ለሚያስፈልጋቸው ነገሮች በመጸለይ።

**በጸሎት የእግዚአብሔርን ፍቅር እንድትናገር እድሎችን የሚፈጥሩልህ ነገሮች:**
1. ጸሎት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ለመጸለይ ዝግጁ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔርን ጠይቅ።

2. እግዚአብሔር እንድትጸልይባቸው የሚያሳይህን ወይም የሚነግርህን የጸሎት ጉዳዮች ጸልይባቸው፤ብትችል ወዲያውኑ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ቅረብ። (ተጨማሪ መግለጫ ለ ተመልከት)

3. በምትጸልይላቸው ጊዜ ሰዎች የሚያነሱትን ጥያቄዎች እና ሐሳቦችን በመጠቀም የእግዚአብሔር ፍቅር ለሌሎች ለማካፈል የምታገኘውን እድሎች ለመጠቀም የተዘጋጀ ሁን።

_ጓደኛ በማድረግ_ እግዚአብሔር እውነት ለሌሎች ለመካፈል ምክር

አንዱ ሰዎችን ጓደኛ የማድረግ ዓላማ የእግዚአብሔርን እውነት እና ፍቅር በየዕለት እንቅስቃሴያችን እግዚአብሔር ወደ እኛ ለሚልካቸው ሰዎች ለማካፈል እድሎችን ይፈጥርልናል።
ዓላማችን የእግዚአብሔርን እውነት እና ፍቅር በየዕለት እንቅስቃሴያችን ለምናገኛቸው ሰዎች ማካፈል ነው።
**ሰዎችን ጓደኛ ማድረግ የሚፈጥርልን ጥቂት እድሎች እንደሚከተሉት ናቸው:**
1. በመጀመሪያ ጊዜ እናገኛቸዋለን።ይህ ብቸኛው ጓደኛ የምንሆንበት እድል ነው፤ምናልባት ለብዙዎች የመጀመሪያ ሊሆን ይችላል።

2. በስራ፤በትምህርት፤በግብይይት ወይም በፕሮግራማችን መሰረት በመደበኛ ሁኔታ ለምናገኛቸው ሰዎች።እነዚህ ነገሮች ጓደኛ ለማድረግ እድሎችን ይፈጥርልናል።

3. እግዚአብሔር በልባችን ባስቀመጠው ሸክም ምክንያት ጓደኛ ልናደርጋቸው በምንችልባቸው ሌሎች መንገዶች መጠቀም።

ሰዎችን ጓደኛ እንድናደርግ እና የእግዚአብሔርን ቃል እንድናካፍል የሚረዱን ነገሮች:
1. ለጠፉ ወዳጆቻችን የጸሎት ዝርዝር ማውጣት (የቤተሰብ አባላት፤ጎረቤቶች፤የስራ ባልደረቦች፤አገልጋዮች፤የቤተክርስቲያን ህብረት ጎብኚዎች ወ.ዘ.ተ) ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ስትናገር በየቀኑ በዝርዝርህ ላይ አዳዲስ ስሞችን ጨምር።በየቀኑ እግዚአብሔር የሰይጣንን ኃይላት ከህይወታቸው እንዲሰብርላቸው ጸልይላቸው (የምትችል ከሆነ) ።እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ወደ ራሱ እንዲያስጠጋቸው እና ስለሐጢያታቸው እንዲወቅሳቸው፤እንዲሁም የውስጥ መሻታቸው በእግዚአብሔር ፊት የቀና እንዲሆን ጸልይላቸው።ኢየሱስን ለመቀበል ያልፈለጉ ሰዎችን እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን የሚያጋጥባቸውን ፍርድ እንዲያሳያቸው ጸልይ።

2. በየዕለቱ ለምታገኛቸው አዳዲስ ሰዎች ሰዎች በተቻለህ መጠን እግዚአብሔርን ፍቅር ስትናገር በፍቅር እንዲሆን ሞክር።ይህ የመጀመሪያ ግንኙነት ከዛ ሰው ጋር የምታገኘው ብቸኛ እድል ሊሆን ይችላል።

3. አንድ ጊዜ ያናገርካቸው ሰዎች ደግመህ የማናገር እድል ሊኖርህ ስለሚችል የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈልን ቀጥልበት።በየዕለቱ ለምታገኛቸው እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ስትጸልይ ቃሉን የምታካፍልበት መልካም አጋጣሚዎችን ታገኛለህ።ያላቀድከው ከጓደኞችህ ጋር የሚኖርህ መገናኘት

ቃሉን እንድትሰብክ እና በሚያስፈልጋቸው ነገር እንድታገለግላቸው እግዚአብሔር ያዘጋጀው መልካም የሆነ መለኮታዊ ቀጠሮ ሊሆን ይችላል፡

4. በየሳምንቱ ቢያንስ በጸሎት ዝርዝር ላይ እግዚአብሔርን ፍቅር ታካፍለው ዘንድ የምትጸልይለት አንድ ሰው ጋር ግንኙነት እንዲኖርህ እግዚአብሔርን ጠይቅ።ጎብኛቸው ወይም ዘና ብላችሁ ስለ እግዚአብሔር የምታውሩበት ጊዜ ይኑራችሁ።ሌላ የሚጸልይልህ አማኝ አብሮህ እንዲሆን ጸልይ።

5. የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ፍቅር በምታካፍልበት ጊዜ ዘና በል፤
ሀ. የእግዚአብሔርን ፍቅር ስታካፍል ከቻልክ እግዚአብሔር ያደረገልህን ነገር አብረህ መስክር።
ለ. የሚቻል ከሆነ በራሪ ወረቀቶችን እና መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ ኪዳን ስጣቸው።
ሐ. እንዲጸለይላቸው የሚያስፈልጋቸው የጸሎት ርዕሶች ካላቸው ቢቻል ሳትለያዩ ጸልይላቸው።

6. ሰውዬው ህይወቱን ለኢየሱስ ከሰጠ እግዚአብሔርን በማወቅ ያድግ ዘንድ እርዳው።

7. ሰውዬው ህይወቱን ለኢየሱስ ካልሰጠ ለሌላ ቀጠሮ በመጋበዝ እና እንደገና እንዲያገኙህ በመጋበዝ ተለያቸው።

*<u>ቤት ለቤት</u> በመሄድ እግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ማካፈል*

ቤት ለቤት በመሄድ እግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ማካፈል ዋና አላማው በተወሰነ ስፍራ ላይ በመሆን ለሁሉም የምስራቹን ወንጌል የማድረስ ተግባር ነው።
ቤት ለቤት በመሄድ እግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ስናካፍል የሚረዱን ቁሰቁሶች፡

1. ምንጎበኛቸውን ቤቶች ስም፤አድራሻ፤እና ሌሎች መረጃዎችን የምመዘግብበት ወረቀት ወይም ማስታወሻ መጻፊያ ደብተር።

2. በራሪ ወረቀቶች።ለቤተክርስቲያን ህብረት ቅርብ ከሆንህ በራሪ ወረቀቶች የሚታደሉበት ጊዜ መረጃ ለማግኘት ለምሳሌ በስብሰባ ጊዜ፤እርዳታ የሚገኝበት እንዲሁም ሌሎችም ነገሮች እነዚህን ቁሳቁሶች ለማግኘት እጅግ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።በግልጽ የተጻፉ መልዕክቶች ለምትጎበኛቸው ሰዎች የምትናገረውን ነገር በሚገባ የሚያብራራ አጋዥ መሳሪያ ነው።በአጭሩ የቀረበ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚናገር በራሪ ወረቀት በእጅህ ላይ ሊኖር ይገባል።

3. ቀለል ያለ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚናገር እና እንዴት ንስሀ እንደምንገባ እና ህይወታችንን ለእግዚአብሔር እንዴት እንደምንሰጥ የሚያብራራ በራሪ ወረቀት ያስፈልጋል።

4. እንዲሁም ሌሎች በተለየ ጉዳይ ለምሳሌ ስለሐይማኖት፤የአደንዛዥ ዕጽ ሱስ፤ወይም የቤተሰብ ችግር የሚያብራሩ በራሪ ወረቀቶች አስፈላጊ ናቸው።

5. መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ ኪዳን ለሌላቸው ሰዎች መስጠት

6. የምስል ወይም የድምጽ ቅጂዎች ተቃሚ ናቸው

ቤት ለቤት በመሄድ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ማካፈል ዋና አላማው የሁሉም ቤተሰብ አባላት ራሳቸውን ለክርስቶስ እንዲሰጡ ይረዳል።

**እግዚአብሔር ትደርሳቸው ዘንድ የሚፈልጋቸው ስፍራዎች ላይ እንድትደርስ የሚረዱህ ደረጃዎች፡**

1. እግዚአብሔር እንድደርስበት ይፈልጋል ብለህ የምታስበውን ስፍራ ካርታ ስራ ወይም ግዛ፡፡
*ማስታወሻ: በመጀመሪያ እግዚአብሔር እንድትደርስበት የሚፈልገው የምትኖርበትን አከባቢ ነው፡፡ካለህበት ስፍራ ጀምር፡፡*

2. በተመሳሳይ ስፍራ ላይ ሸክም ካላቸው ሰዎች ጋር ቡድን መስርተህ ተንቀሳቀስ፡፡

3. ቡድኑ ሊደርስበት የሚፈልገውን ስፍራ በወንጌል ለመድረስ ከመጀመሩ በፊት በመንፈሳዊ ኃይላት ላይ አቅም ለመስበር እንዲሁም እግዚአብሔር እንዲቀባቸው እና ጥበብ እንዲሰጣቸው በጾም እና በጸሎት መጀመር አለባቸው፡፡በየስፍራው እየተዘዋወሩ እና በየቤቱ እየገቡ ለምስራቹ ወንጌል ክፍት እንዲሆኑ መጸለይ አለባቸው፡፡ይህ የፀሎት ጉዞ ይባላል፡፡

የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፤አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).

4. የቤት ለቤት ጉብኝት ጀምር፡፡ሁሉንም ቤት እየተመላለስክ ጎብኝ፡፡ሰዎች ቤታቸው የሚሆኑበትን ጊዜ እወቅ፤ቀስቅሰቸው፤ምግብ አትብላ፡፡ከመሻ በኋላ ለጉብኝት መውጣት በአንዳንድ ስፍራ ላይ አይመከርም፡፡

5. ቤት ለቤት እየሄድን ቃሉን የምናካፍልበት ዘዴዎች:
a. የበር ደውል ካለ ደውል፡፡ከሌለ እንዲሰማ አድርገህ አንኳኳ፤ከዛም ለ30 ሰከንድ ወይ ከዛ በላይ ቆይ፡፡መልስ ከሌለ ለተጨማሪ ጊዜ አንኳኳ፡፡እስኪመልሱ ድረስ ጊዜ ስጣቸው፡፡አሁንም መልስ ከሌለ ስማቸውን፤አድራሻቸውን፤ቀኑን፤እና ሌላ ለቤት ለቤት አገልግሎትህ ጠቃሚ መረጃ የሚሆን ካለ መዝግብ፡፡
ለ. ሰው በቤት ካለ:
(1) እራስህን አስተዋውቅ
(2) አከባቢውን የምትጎበኘው ለአከባቢው ህዝብ ጥቅም እንደሆነ በማሳወቅ እውነታውን አስረዳ፡፡
(3) እንዲናገሩ ፍቀድላቸው፡፡ስለ ስራቸው፤ቤተሰቦቻቸው እና ሌሎች ነገሮች በተመለከተ የተለመደ ጥያቄ ጠይቃቸው፡፡
(4) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልትጠይቃቸው ትችላለህ:
(ሀ) ለምን ያህል ጊዜ በዚህ ኖራችሁ?
(ለ.) የትኛው ሐይማኖት ተከታይ ነበራችሁ?
(ሐ) በአሁኑ ጊዜ ከአንድ ሐይማኖት ህብረት ውስጥ ትካፈላላችሁን?
(መ) ለህይወት ችግሮች መፍትሔ ላካፍል እችላለሁን?
(5) እድሉን ስታገኝ በራሪ ወረቀት ወይም በትምህርት 3 ላይ የተጠቀሰውን ርዕሰ ጉዳይ በመጠቀም ስለ እግዚአብሔር ፍቅር አስተምር፡፡
(6) ቤተሰቡ የሚያስፈልገውን የመንፈሳዊ ፍላጎት ለማወቅ ሞክር፡፡<u>ቤታቸውን ለቀህ ከሄድክ በኋላ</u> በያዝከው ወረቀት ወይም የማስታወሻ ደብተር ላይ ትመዘግበዋለህ፡፡
(7) የእግዚአብሔር ፍቅር መልዕክትን የሚቀበሉ ከሆነ በትምህርት 7 የተጠቀሱትን የክትትል ሂደት ተጠቀም፡፡
(8) የእግዚአብሔር ፍቅር መልዕክትን የማይቀበሉ እንኳ ቢሆን፤ነገር ግን እድሉን ለሚቀጥለው የአገልግሎት ጊዜ ክፍት አድርገህ ተለያቸው፡፡
(9) ሁልጊዜ በጸሎት ለመዝጋት ሞክር፡፡የተለየ የጸሎት እርዳታ የሚያሻቸው ከሆነ ጠይቃቸው፡፡
ሐ. ማንም ሰው በቤት ውስጥ ከሌለ:
*ልትጎበኛቸው መጥተህ እንዳጣሀቸው የሚገልጽ <u>ግልጽ የሆነ መልዕክት አስቀምጥላቸው</u>፡*የሚያስፈልጋቸውን ነገር ልትሰጣቸው እንዳሰብክ መልዕክቱ እንደሚነግራቸው እርግጠኛ ሁን፡፡ሌላው መልዕክቱ ለሚያስፈልጋቸው ነገር ትጸልይላቸው ዘንድ ሊያገኙህ እንደሚችሉ ይነግራቸዋል፡፡

*በየዕለቱ እና ቤት ለቤት እየሄድክ ለምታገኛቸው ሰዎች የእግዚአብሄርን የምስራች ወንጌል ለማካፈል የሚረዱ መመሪያዎች*

1. ሁልጊዜ ፈገግታ የማይለይህ፤ትሁት እና ጨዋ ሁን፡፡ስለ ሰጡህ ጊዜ አመስግናነቸው፡፡
2. ሁልጊዜ ሲጠይቁህ በተረጋጋ ሁኔታ አዳምጣቸው፡፡ (ፈገግ በል፤በራሪ ወረቀት ስጣቸው፤ስለሰጡህ ጊዜ አመስግናነቸው)
3. *<u>ቤታቸውን ለቀህ ከሄድክ በኋላ እና ወደ ሌላ ቤት ከመግባትህ በፊት</u> ሁልጊዜ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ምላሻቸውን እና ሌሎች መረጃዎችን መዝግብ፡፡*
4. በተቻለህ መጠን በጥሩ ሁኔታ ልበስ፡፡
5. ቢቻል ሁለት ሁለት የተጋቡ ጥንዶች ቢሄዱ መልካም ነው፡፡የተጋቡ ጥንዶች ከሌሉ እንደ ቡድን ሦስት ሆናችሁ ሂዱ፤አንዱ ተቃራኒ ጾታ ይሁን፡፡
6. ልጅ የሚመልስ ከሆነ ለአባታቸው ወይም እናታቸው እንዲናገሩ ጠይቁ፡፡
7. በር ላይ ቆመህ ስትጠብቅ ከበሩ ትንሽ ራቅ ብለህ ቁም፤ምንም አትናገር ምክንያም አንድ ሰው ሊመለከትህ ይችላል፡፡
8. ስትሄዱ በመሀከላችሁ ንግግር አይኑር፡፡ እንደምትሰማ እርግጠኛ እስክትሆን ድረስ አትናገር፡፡
9. ለጎበኘሀቸው ሰዎች ሁልጊዜ ጸልይላቸው፡፡
10. ከጉብኝት ከተመለስህ በኋላ ለቡድኑ ለወደፊት ጉብኝታችሁን እንደምታሻሽሉ ንገራቸው፡፡
11. በመጀመሪያ ጉብኝታችሁ የምትጎበኟቸው ሰዎች ጊዜ እንደሌላቸው ከነገሯችሁ ለሚቀጥለው ስትመለሱ ቁርጥ ያለ ጊዜ እንዲሰጧችሁ ጠይቁ፡፡የሰጧችሁን ጊዜ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ መዝግቡት፡፡
12. ሁልጊዜ በየቤቱ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚገልጽ ጽሁፍ ወይም የድምጽ ቅጂ አስቀምጥ፡፡
13. የእግዚአብሔርን ፍቅር መልዕክት ለመስማት ዝግጁ እስከሆነ ድረስ ሁልጊዜ መጎብኘትን ቀጥልበት፡፡

ህይወታቸውን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ከወሰኑ በትምህርት 7 ላይ የተጠቀሱትን የክትትል ሂደት ተጠቀም፡፡

*የእግዚአብሔርን የምስራቹን ወንጌል መልዕክት ለምን እንሰብካለን*

1. ለምናገኛቸው ሰዎች የመስራቹን ወንጌል መስበክ ክርስቲያናዊ ባህላችን መሆን አለበት፡፡
2. ለመስበክ ውጤታማ የሆነው - ወላጆች ለልጆቻቸው, ጓደኛ ለጓደኛ, ጎረቤት ለጎረቤት, ሰራተኛ ለሰራተኛ, እርስ በእርስ የመስራቹን ወንጌል በሚገባ ይሰበካል፡፡
3. ወንጌልን ለማካፈል አጋዥ ነው - መውደድ፤ግንኙነትን መንከባከብ, ሰዎች እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ መርዳት ያስፈልጋል፤ወንጌልን እንደ ጓደኛ ሆነን ስናካፍል መልካም ነው፡፡
4. ለመስበክ ደስተኛ እና በሀሴት የሚሞላው - ታላቁ በግል የሚሰጠው ሽልማት- ቤተሰብህን፤ጓደኞችን፤ጎረቤቶችህን፤የስራ አጋሮችህን እና ሌሎችንም ወደ እግዚአብሔር ሀሳብ መምራት ነው፡፡

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. በየዕለት ህይወትህ የምታገኛቸውን እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ዝርዝር ጽፈሀልን? አዎ__ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ አሁን ያድርጉት፡፡
2. ለጸሎት ዝርዝርህ ሁልጊዜ ትጸልያለህን? አዎ__ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ አሁን ጀምር፡፡
3. ባገኘሸው አጋጣሚ የመስራቹን ወንጌል ለሰዎች ትሰብካለህን እንዲሁም ትጸልያለህን? አዎ__ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ አሁን ጀምር፡፡
4. የምታውቃቸውን 12 ጎረቤቶችህን መንፈሳዊ ሁኔታ ታውቃለህን? አዎ__ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ አሁን ለማወቅ ወስን፡፡

*የተግባር ሥራ*: በዚህ ሳምንት በማስታወሻ ደብተር ዝርዝር ላይ የሚገኘው ልትመሰክርለት ላለው መስክር፤እንዲሁም ስላልሆነው ነገር ሁሉ ግልጽ የሆነ ታሪክ ጻፍ፡፡

# ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መናገር
# ትምህርት 7
# ክትትል

የምታሰላስሉት ማስታወሻ: ርዕሰ ጉዳዩን በማንበብ፤አሰላስለው (የሚለውን እና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርገው አሰላስል).

ሰዎች እግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ወዳጅትን ይመሰርቱ ዘንድ ወይም አዲስ አማኞች በቤተክርስቲያን ያላቸው ህብረት ይጠነክር ዘንድ ታላቅ ወንድም እና እህት ሁን።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ አዲስ ቤተቦችን በመቀበል ወይም በወንጌል የምደትርሳቸውን ቤተሰብ በመቀበል ምራ።

**የክትትል ዓላማ**: አዲስ አማኞች እግዚአብሔር በማወቅ ያድጉ እና በህይወታቸው የእግዚአብሔር ዓላማ ይፈጽሙ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ወዳጅትን ይመሰርቱ ዘንድ ነው።

**የክትትል ግብ**: ለአዲስ አማኞች የሚከተሉትን ለመመስረት ነው፤

1. የየዕለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
2. የየዕለት ጸሎት
3. የውኃ ጥምቀት
4. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ህይወት
5. ከሌሎች አማኞች ጋር ያለ ህብረት
6. የእግዚአብሔር ፈቃድ በህይወታቸው ይፈልጉ ዘንድ

**ከአዲስ አማኞች ጋር በመሆን እነዚህን ደረጃዎች አጥናቸው**:

1. ከአዲስ አማኞች ጋር ግንኙነት ፍጠር።ደውልላቻው ወይም ጎብኛቸው (የሚቻል ከሆነ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ) መጽሐፍ ቅዱስን እንድታካፍሉ እና ግንኙነታችሁን ይበልጥ ለማጠንከር የምትገናኙበትን ጊዜ ወስኑ።

2. መጽሐፍ ቅዱስን ማፋከል ጀምር።በመጀመሪያ ጉብኝትህ "በየዕለት ህይወትህ እግዚአብሔር በማወቅ እንዴት እናድጋለን" የሚለውን የመጀመሪያውን ትምህርት 1 አስተምር።

3. ከሌለች አማኞች ጋር ወደሚደረግ ስብሰባ ጋብዛቸው ወይም ይዘሃቸው ሂድ።

4. የሚቻል ከሆን በደንብ እስኪጸኑ ድረስ በሳምንት ሁለት ጊዜ አግኛቸው።

5. በየዕለቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚሆኑበት ጊዜ እንዲኖራቸው፤የውኃ ጥምቀት እንዲወስዱ፤በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ህይወት እንዲኖራቸው፤የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለህይወታቸው እንዲፈልጉ አበርታቸው።

6. ለመምከር እና በሚያስልጋቸው ነገር ለመርዳት እራስህን አዘጋጅ።

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

በዚህ ክፍል የተሰጠውን የክትትል መመሪያ በአግባቡ እየተጠቀምክበት ነውን? ትጸልያለህን? አዎ__ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ አሁን ጀምር።

**ተግባራዊ *ሥራ***: የተሰጠውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የምትመራቸውን ሰዎች ማስተማር ጀምር።

## ተጨማሪ መግለጫ ሀ
## የጸሎት የቀን ማስታወሻ እንዴት እንደምናዘጋጅ የሚያስተምር መመሪያ

1. ሁልጊዜ በዚያ ቀን ስለ አደረከው ዋና ነገር በተለይ የእግዚአብሔርን ቃል ለማካፈል ስለገጠመህ እድሎች እና ስለ ተመለሰልህ የጸሎት መልስ ጻፍ።ስላገኘሀቸው ሰዎች፣ስለወሰንከው ውሳኔ፣ስለ ነበረህ ሀሳብ፣ስለሆነው መልካም እና መጥፎ ነገሮች ግልጽ የሆነ ጽሁፍ አዘጋጅ እንዲሁም ያደረከውንሁሉ ገምግም።እንዴት እንደምታሻሽልው እና ስህተቶችን እንዴት እንምታስወግድ ጻፍ።

ለምሳሌ: ጥር 3, 1992
ወደ ስራ ሄድን።እጸልይለት ለነበረው ዮሐንስ የምስራቹን ወንጌል፣ኢየሱስን አካፈልኩት።በጸሎት ዝርዝሬ መሰረት ጸለይኩኝ፣እንዲሁም በማቴ 24 ላይ ስለሚገኘው መጨረሻ ዘመን በቂ የሆነ መረዳትን አገኘሁ (የጥናት ጽሁፉን ይመልከቱ) ።ለተለየ የገንዘብ አቅርቦት ጸለይኩኝ። (የጸሎት ገዞ የሚለውን ተመልከት)

2. በተለያዩ ክፍሎች የተከፋለ የጸሎት ዝርዝር አውጣ፣የጠፉ ነፍሳት፣የቤተክርስቲያን አባላት፣የፖለቲካ እና መንፈሳዊ መሪዎች፣ሚሲዮናውያን፣እና ልዩ የሆኑ የሚያስፈልጉን ነገሮች።

ምሳሌ :
የጠፉ ነፍሳት፣የቤተክርስቲያን አባላት፣መሪዎች፣ሚሲዮናውያን፣ልዩ የሆኑ ፍላጎቶች
ጄ.ሽርሊ ጋየል መጋቢ (የወንጌል ተልዕኮ ገዞ ስም.ፕሬስ.ቡሽ ሚሲዮናዊ)

3. ለተለየ የጸሎት ጥያቄ የጸሎት ገዞ አድርግ; የጸሎት ጥያቄ፣የተደረገበት ቀን፣መች እንደተመለሰ እና እንዴት እንደተመለሰ።

4. እግዚአብሔር በየዕለት ህይወትህ ባሳየህ መሰረት ለየት ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ገዞ አዘጋጅ።

ምሳሌ:
ማቴ 24
ጥር. 3, 92
ቁጥር 14 ኢየሱስን መስበክ ምን የህል አስፈላጊ እንደሆነ አሳየኝ።
ቁጥር 20 እና 21 ጸሎት ምን የህል አስፈላጊ እንደሆነ አሳየኝ።
ቁጥር 44 - 51 እግዚአብሔር ያዘዘኝን ማድረግ ምን የህል አስፈላጊ እንደሆነ አሳየኝ።

# ተጨማሪ መግለጫ ለ
# የግል የጸሎት ዝርዝር

1. የእግዚአብሔርን ፍቅር ያልቀመሱ ሰዎች፤ቤተሰብ፤ጎረቤት፤የስራ ባልደረባ/የክፍል ጓደኛ እና ሌሎችም

2. የኢየሱስ ተከታዮች

1. መሪዎች

2. ሚሲዮናውያን

3. ልዩ ፍላጎቶች

4. ሌሎች የጸሎት ጥያቄዎች

# ተጨማሪ መግለጫ ሐ
# ልብን የሚመረምር ጸሎት
# ለመንፈሳዊ መነቃቃት እና ለውጥ

መዝ 139:23-24: "አቤቱ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ ፍተነኝ መንገዴንም እወቅ
በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ።."

ሐጢያትን መናዘዝ ከእግዚአብሔር ለሚኖረን ህብረት እና በእግዚአብሔር ህዝብ መሀከል ለሚኖር መነቃቃት እጅግ በጣም አአስፈላጊ ነው።የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጸሎት ተመልከታቸው።ጥያቄዎቹን አንድ በአንድ ተመልከታቸው።
ሁሉንም ጥያቄዎች በእውነት መልሳቸው ሁሉም "አዎ" የሚሉ መልሶች ሀጢያት በህይወት ውስጥ አለ ማለት ነው።
እነዚህን መጠይቆች በማንበብ፤ስለሐጢያትህ ስትወቀስ፤ለእግዚአብሔር ስትናዘዝ፤በአግባቡ ስትመላለስ...ከዛም መንጻት እና የሐጢያት ይቅርታ መጠየቅ ትችላለህ።

1 ዮሐ 1:9 "በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።"ሐጢያትህን ለእግዚአብሔር መንገርህን እርግጠኛ ሁን...."ጌታ ሆይ በእቅዴ ውስጥ የመጀመሪያውን ሥፍራ አልሰጠሁም."ወይም ."ጸሎት እና የአንተን ሥራ ቸል ብያለሁ."
በህይወትህ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም አይነት ሐጢያት ለማወገድ ቸል አትበል።ምሳ 28:13: "ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።"
ሌሎች ቢሰሩትም ወይም ባይሰሩትም፤ክርስቲያን ምንም ያልተሰራ ሥራ መተው የለበትም።እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ታላቅ የሆነ መንፈሳዊ መነቃቃትን ሊያመጣ ይፈልጋል።እሱ ማንኛውንም መንፈሳዊ ስራ በመንፈስ ቅዱስ እና በቃሉ ተጠቅሞ በአንተ ውስጥ መስራትን ይፈልጋል።ከፈለከው በእግዚአብሔር ህልውና የሚረጋገጥ መነቃቃት ዛሬ በአንተ ይጀምራል።
መጀመሪያ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሚገባ አንብባቸው እና እውነተኛ የሆነ መልስ "አዎ" ወይም አይደለም" በማለት መልስ።

1. <u>ማቴ 6:12-15:</u> ቂም የያዝክበት ሰው አለን? ይቅር ያላልከው ሰው አለን? የምትጠላው ሰው አለን? የማትወደው ሰው አለን? ይቅር እንዳትል እና በደልህን እንዳትረሳ የሚያደርግህ አለመግባባት አለን? ሰውን ልትጎዳ በውስጥህ ደብቀህ የያዝከው ምሬት እና ቁጭት አለን? ሲያመሰግን ወይም ሲናገር ስትሰማው የምትጠላው ሰው አለን? በሌሎች ላይ የተሳሳተ አመለካከት እንዲኖር ለራስ ትፈቅዳለህን?

2. <u>ማቴ 6:33:</u> እግዚአብሔርን ያላስቀደምክበት ነገር አለህን? እግዚአብሔርን ከመፈለግ እና ፈቃዱን ከመከተል ይልቅ በራስህ ጥበብ እና ምኞት ውሳኔ ወስነህ ታውቃለህን? የሚከተሉትን በማንኛውም መንገድ በአገልግሎትህ እና ህይወትህ ጣልቃ የሚገቡት የትኞቹ ናቸው?
እግዚአብሔር: ምኞት, ደስታ, ማፍቀር, ዝነኛ የመሆን ምኞት, ገንዘብ, የራስህ እቅድ?

3. <u>ማር 1:17:</u> የጠፉ ነፍሳትን መፈለግ አቁመሀልን? በአንደበትህ ስለኢየሱስ ክርስቶስ በቀጣይነት መመስከር አቁመሀልን? ህይወትህ ወደ ክርስቶስ ላልመጡ ሰዎች ምሳሌ ሊሆን አይደለም?

4. <u>ዮሐ 13:35:</u> ሰዎች በሚያጋጥማቸው መጥፎ ነገሮች በውስጥህ ትደሰታለህን? በሌሎች ስኬት ወይም መሻሻል በልብህ ትናደዳለህን? በማኛውም አላስፈላጊ ክርክር ውስጥ አለህበትን? መልካም ባልሆነ ጠብ፣ክርክር ውስጥ ትሳተፋለህን? የማንኛውም መከፋፈል ውስጥ አባል ነህን? ሆን ብለህ ፊትህን ያዞርክባቸው ሰዎች አሉን?

5. <u>ሚል 3:10:</u> ጊዜህን፤ችሎታህን እና ገንዘብህን ለእግዚአብሔር ባለመስጠት እግዚአብሔርን ሰርቀሀልን? ከምታገኘው ገቢህ ከአስር እጅ በታች ለእግዚአብሔር ትሰጣለህን? የእግዚአብሔርን ስራ በጸሎት እና በገንዘብ አትደግፍምን?

6. <u>1 ቆሮ 4:2:</u> ታማኝ ባለመሆንህ ለእግዚአብሔር ሥራ ሀላፊነት ለመቀበል አትታመንምን? በስሜት ተነሳስተህ እግዚአብሔርን ሥራ ትበጠብጣለህን ነገር ግን አንተ የምትሰራው ምንም ነገር የለምን?

7. <u>1ቆሮ 6:12-20:</u> የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ በሆነው ስጋህ ላይ ቸልተኛ ነህን? የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ በሆነው ስጋህ ትጠነቀቃለህን? በመብል እና በመጠጥ እራስህን መቆጣጠር ይሳንሀለን? ሰውነትህን የሚያረክስ ልማድ አለብህን?

8. <u>1 ቆሮ 10:31:</u> በህይወትህ ከሚያጋጥሙህ መልካም ነገሮች ለእግዚአብሔር ክብር ከመስጠት ይልቅ በራስህ ጥረት እንዳገኘኸው በማሰብ እራህን ታመሰግናለህን? ክርስቶስ ከሰራው ስራህ የልቅ ራስህን ስራ ተጎላለህን? ሁልጊዜ ስትናገር "እኔ" ማለት ይቀነሀልን? ስሜትህ በቀላሉ ይጎዳልን? ያልሆንከውን ነገር እንደሆንህ አድርገህ ታስመስላህን?

9. <u>ኤፌ 3:20:</u> ክርስቶስን ማዕከል ከማድረግ ይልቅ እራስህን ማዕከል ታደርጋለህን? ጌታን እንዳታገለግል ምክንያት የሚሆንብህን የበታችነት ስሜትን ትፈቅዳለህን?

10. <u>ኤፌ 4:28:</u> ለሰራተኞችህ በቂ ደሞዝ አትከፍልምን? በስራህ ቸልተኛ ነህን? እዳህን ለመክፈል ቸልተኛ ሆነሀልን? እዳህን ላለመክፈል ታቅማማለህን? የሌሎችን ጊዜ ታባክናለህን?

11. <u>ኤፌ 4:31:</u> ታማርራለህን? በውሀ ቀጠነ ጥቃቅን ችግሮችን የምትፈልግ ነህን? በማንኛውም ሰው ወይም ነገር ላይ የትችት አመለካከት አለህን? ተናዳጅ ነህን? የተደበቀ ንዴትን በውስጥህ ትይዛለህን? ትናደዳለህን? በሌሎች ላይ ትዕግስተኛ አይደለህምን? መልካም ያልሆነ ባህሪ አለብህን?

12. <u>ኤፌ 5:20:</u> በመልካምም ሆነ በክፉህ በሚያጋጥምህ በማንኛውም ጊዜያት እግዚአብሔርን ለማመስገን ቸል ትላለህን? የእግዚአብሔርን ቃል በመጠራጠር እግዚአብሔርን ውሽታም ብለህ ጠርተው ታውቃለህን? ትጨነቃለህን?

የመንፈሳዊህ ነገርህ የሚለካው ባለህበት ወቅታዊ ስሜትህ ነው ወይሥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ነው?

13. ኤፌ 5:16: እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆኑ የሬዲዮ እና የቴሌቪዢን ፕሮግራሞችን ትከታተላለህን? ያልተገባ መጽሔቶችን ታነባለህን? ዓለማዊ የሆኑ መዝነኛዎችን ላይ ትካፈላለህን? ከማንኛውም ጥያቄ ከሚያስነሳ ምንጭ ደስታን ማግኘት ትፈልጋለህን? በኢየሱስ ክርስቶስ ደስተኛ አለመሆንህን የሚያሳይ ነገሮችን ታደርጋለህን?

14. ፊሊ 1:21: ስለ ህይወትህ ታስባለህን? ከሰዎች ጋር የሚኖርህ ንግግር ጊዜያዊውን ደስታ ለማራካት በዓለማዊ ነገሮች ላይ ነው ወይስ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ቃሉን መሰረት ያደረገ ነው? ምድራዊ ነገር ከኢየሱስ ይልቅ ያስደስትሀልን?

15. ፊሊ 2:14: በቃል ወይም በድርጊት ሌሎችን መጉዳት ትፈልጋለህን? ታማህን? ሰዎች በሌሉበት ስለ እነሱ በጥፎ ነገር ታወራለህን? እውነተኛ ክርስቲያኖች ላይ ቂም ትይዛለህ ምንያቱም እነሱ ከእናንተ የተለየ ስለሆኑ እና እናንተ የምታርጉትን ስለማያደርጉ?

16. ፊሊ 4:4: እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ ለማስደሰት ቸል ትላለህን? በእግዚአብሔር ላይ ታጉረመርማለህን? በማንኛውም አጋጣሚ በእሱ ላይ ታማርራለህን? እሱ በሚሰጥህ ስጦታዎች ደስተኛ አይደለህምን? ለእግዚአብሔር በሙሉ ልብህ ለመታዘዝ ፈቃደኛ አይደለህምን? እንደ ፈቃዱ መሰረት የምትሰራውን ወይም የማትሰራውን በተመለከተ ገደብ አለህን? የሱን ምሪት አትታዘዝምን?

17. ቆላ 3:5-9: ረብ የሌለው እና ፍሬ ቢስ የሆነ ወሬ ታወራለህን? ትዋሻህን? ታጋንናለህን? ታታልላለህን? ትሰርቃለህን? በጥንቃቄ አስተውል....ከመጠን በላይ ሰው ትጫናለህን?

18. 2 ጢሞ 2:22: ያልጸዳ ግላዊ ባህሪ አለብህን? ተቃራኒ ጾታን በተመለከተ እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆነ ቆሻሻ አስተሳሰቦችን ወደ አዕምሮ እንዲገቡ ትፈቅዳለህን? እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆኑ ያልጸዱ እና ቀሻሻ አመለካከቶችን የሚያራምዱ ጽሁፎችን ታነባለህን? ያልጸዱ የመዝኛና ዝግጅቶች ውስጥ ትሳተፋለህን? በዓለማዊ ምኞት ትሳባለህን?

19. ዕብ 10:25: የምስራቹን ወንጌል ለሚጠፉ ነፍሳት ለማድረስ በሚደረግ ስብሰባ ላይ ትቀራለህን? የእግዚአብሔር ቃል ሲሰበክ ወይም ሲነበብ ሌላ ነገር ታስባለህን? በወንጌል አገልግሎት ላይ መደበኛ የሆነ ተሳትፎ የለህምን? በጸሎት ፕሮግራሞች ላይ በሚገባ አትሳተፍምን ወይም ቸል ትላለህን? የግል የጸሎት ፕሮግራም ለመያዝ ቸል ትላለህን? የእግዚአብሔር ቃል ቸል ትላለህን? መጽሐፍ ቅዱስ እና ጸሎት ለአንተ የማያስደስት ነገር ነውን? ለማዕድ ስትቀርብ ለማመስገን ቸል ትላለህን? የቤተሰብ አብሮ የመጸለይ እና ቃሉን የማጥናት ፕሮግራምን ቸል ትላለህን?

20. ዕብ 13:17: በቤተክርስቲያንም ሆነ በሌላ ስፍራ ለሽማግሌዎች ለመታዘዝ ፈቃደኛ አይደለህምን? ሰነፍ ነህን? ለወንጌል ሥራ ድጋፍ እንድታደርግ ስትጠየቅ ትቃወማለህን? ግትር የሆነ ወይም ለመማር ፈቃደኛ ያልሆነ መንፈስ አለህን?

21. ያዕ 1:27: በዓለም የረከስክ ሆነህ እራስህን አግኝተዋለህን? የአለባበስ ሁኔታህ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነውን? ጊዜ እና ገንዘብህን እግዚአብሔርን በሚያስደስት ነገሮች ላይ ታውላለህን? ስለምትገዛቸው ነገሮች ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለህን?

22. ያዕ 4:6: የአኗኗር ዘይቤህ እንደ ክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነውን? መልካም ነህን? ግትር ነህን? በራስህ ማስተዋል ትደገፋለህን?

23. *ያዕ 4:11:* *ጌታን አታከብርምን፣እንዲሁም አገልጋዮቹን በመተቸት ስራውን ታደናቅፋለህን? ለመጋቢህ ወይም ሌሎች መንፈሳዊ መሪዎች መደበኛ በሆነ ሁኔታ ለመጸለይ ደክመሀልን? ለመገሰጽ እና ከጥፋትህ ለመመለስ ግትር ነህን? ሊገስጽህ በመጣው ሰው ተቃውሞ ታስነሳለህን? እግዚአብሔርን ከሚያስደስት ነገር ይልቅ ሰዎች ምን ይላሉ ብለህ ትጨነቃለህን?*
*ታማኝ እና ሐጢያትህን ለማመን እውነተኛ ከሆንህ፤እንግዲህ ለእግዚአብሔር የመንጻት ስራ ዝግጁ ነህ ማለት ነው።የተቀበልከው ሐጢያት ንስሀ የገባህበት ነው።*
እነዚህን ሦስት ነገሮች አስታውስ:
1. እግዚአብሔርን የማያስደስት ሐጢያት ካለብህ፤ለእግዚአብሔር ተናዘዝ፤ከዛም ከእግዚአብሔር ያለህን ግንኙነት አስተካክል።
2. ሌላው ወገንህን የሚጎዳ ሐጢያት ካለብህ፤ለእግዚአብሔር ተናዘዝ፤ከዛም ከዛ ወንድምህ ጋር ያለህን ግንነኙነት አስተካክል።
3. ሌሎችን በርካታ ሰዎች በአንድነት የሚጎዳ ሐጢያት ካለብህ፤ለእግዚአብሔር ተናዘዝ፤ከዛም ከሰዎቹ ጋር ያለህን ግንነኙነት አስተካክል።
**ከልብ የሆነ እና ሙሉ የሆነ መናዘዝ ካለ፤ሙሉ የሆነ መንጻት ይኖራል።የእግዚአብሔር ደስታ ይመጣል፤ከዛም ምስክርነት ይመጣል እንዲሁም በመንስ ቅዱስ የሆነ ጸሎት ይኖራል፤ከዛም መነቃቃት ይኖራል።**
*መዝ 19:12; "ስሕተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ።"*
**ይህ የጸሎት ዝርዝር በሻን ቱንግ፣ቻይና ለሚገኙት ቅዱሳን በ1930 ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ነው።እግዚአብሔር ለሰጣቸው መታዘዝ ሲጀምሩ ተላቅ የሆነ መነቃቃት መጣ፤ሰዎች ዳኑ፤ተፈወሱ፤ከሰይጣን እስራት ተፈቱ፤ከሞት ተነሱ።**

# ተጨማሪ መግለጫ መ
# ለጸሎት እርምጃ መመሪያ
# ለአከባቢ እና ለሰዎች የሚደረግ የምልጃ ጸሎት መመሪያ

## ጀምር
በጸሎት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህ ጸልይ

## ወደ ህልውናው ግባ
በምስጋና እና በአምልኮ ወደ ህልውናው ግባ። የምትችል ከሆነ የምስጋና እና የአምልኮ መዝሙር ዘምር።

## እንቅፋቶችን አስወግድ
በጸሎት ህይወትህ ላይ እንቅፋት ሊሆን የሚችል ማንኛውንም አይነት ነገሮች እግዚአብሔር እንዲያሳይህ ጸልይ።ወደ ምልጃ ጸሎት ከመሄድህ በፊት በተጨማሪ መግለጫ ሐ ላይ ያለውን የለወጥ ጸሎት የሚለውን ተመልከት።

## ማልድ:
የጸሎት ጊዜ ዋና ዓላማው የምታገለግላቸው ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል ልባቸውን እንዲያዘጋጁ ነው።

## ስትጸልይ የሚከተሉትን መመሪያዎች በሚገባ ተጠቀምባቸው:
እግዚአብሔርን በከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዞች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ላይ ስልጣንን ስለሰጠህ አመስግን።
**በየዕለት ህይወትህ እና አገልግሎት በምታገናቸው ሰዎች፤በቤተሰብህ፤እንዲሁም በአንተ ላይ የኢየሱስን ደም እርጭ።**

**ጠላት ዲያቢሎስን እየተቃወምህ ጸልይ**፤ተፈጥሮው እና ባህሪው የሆኑት ባለጋራ፣ሌባ፣ነፍሰ ገዳይ እና የውሸት አባት፣አታላይ፣ሐሰተኛ የብርሃን መልአክ፣የዚህ የጨለማው ዓለም ገዢ እና አምላክ እንዲሁም በአየር ላይ ገዢ እና ኃይላትን ተቃወም።

**የምትጸልይላቸው ሰዎች እና ስፍራዎች በምስራቹ ወንጌል እንደሚደረሱ አውጅ።እነሱ** የእግዚአብሔር መንግስት አባል እንደሚሆኑ በኢየሱስ ስም አውጅ።የእግዚአብሔር ቃል በምድር ላይ የረገጥነውን ስፍራ ሁሉ እንደሚያወርሰን ዓለምን ለእርስታችን አሳልፎ እንደሚሰጠን ይናገራል። ህዝቡ የእግዚአብሔር መንግስት አባላት እንዳይሆኑ የሚገዳደሩ **እርኩሳን መናፍስትን ተቃወሙ**፤"በኢየሱስ ስም እሰሯቸው"; የሐይማኖት መናፍስት, ዓለማዊ ምኞት, የሰዎች ባህል, ግራ መጋባት,የጭፈራ መናፍስት፣ነፍሰ ገዳይ መንፈስ፣ግብረሰዶማነት፣እና ቆሻሻ አመለካከት፣ቁማርተኝነት፣የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ እና ሌሎችም እግዚአብሔር የሚገልጥልንን መናፍስት እንቃወም።

**መንፈስ ቅዱስ ህዝቡን ስለ ሐጢያቱ እንዲወቅሰው እና መሻቱ እና ፍላጎቱ እንደ** እግዚአብሔር ቃል እንዲሆን ጸልይ፤እንዲሁም እግዚአብሔር ቃል የማይሰሙ ከሆነ የዘለዓለም ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ንገራቸው።

የዘለዓለማዊ ደህንነት ወራሾች የሚሆኑ ሰዎችን እንዲያመጡ እግዚአብሔር የሚያገለግሉ መልዓክን እንዲለቅ ጸልይ።

የእግዚአብሔር ሰዎችን የማዳን ስራ እንዳይሰራ ወይም የምትጸልይላቸው ወገኖች እንዳይድኑ ሰዎች ክፋት እና በደል ይፈጽሙ ዘንድ የሚያነሳሱትን መናፍስት የሚዋጉ መልዓክን እግዚአብሔር እንዲለቅ ጸልይ።

ሰዎችን በወንጌል ስታገለግል ምልክቶች፤ድንቆች እና ታእምራት ትሰራ ዘንድ እግዚአብሔር ሰማይን መስኮት እንዲከፍት ጸልይ።

ሰዎችን በወንጌል ስታገለግል የእግዚአብሔር ሰላም እና ፍቅር እንዲመጣ ጸልይ።

ሰዎችን በወንጌል በምታገለግልበት ስፍራ እና ሰዎች ላይ **መንፈሳዊ መነቃቃት እና መለወጥ** እንዲመጣ እና የእግዚአብሔር መንግስት እንዲመሰረት ጸልይ።

የምትጸልይላቸው ስፍራዎች ወይም ሰዎችን ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር በወንጌል ስትደርስ **የመንፈስ ቅዱስ ህብረት እና አንድነት እንዲመጣ ጸልይ**፡ማንኛውም አይነት ከእግዚአብሔር ያልሆነ ባህል፤መከፋፈልን የሚያመጣ የሰዎች ምኞት፤ውሸት እንዲሰበር ጸልይ።ፍቅር፤ጸሎት፤አምልኮ፤ስብከት፤ደቀመዝሙር ማፍራት፤ወንጌል ማገልገል፤እና የወንጌል ሰባኪነት በቤተክርስቲያን ህብረት ውስጥ እንዲያድግ ጸልይ።

**ቡድኑ የሚረዳቸው የአንድ አከባቢ ወይም የህዝብ አለማዊ ወይም የሐይማኖት መሪዎች በጽድቅ እና በስርዓት እንዲመሩ ወይም እንዲወገዱ ጸልይ።**

**ለመኸሩ የሚሆኑ ሰራተኞች እንዲነሱ ጸልይ።** አንተ ለምትጸልይባቸው ስፍራዎች እና ህዝቦች የሚያገለግሉ አገልጋዮችን እግዚአብሔር እንዲያስነሳ ጸልይ።የኢየሱስን ወንጌል የሚሰብኩ እና ለክርስቶስ የሚኖሩ ወንዶች እና ሴት ወገኖች እንዲሆኑ ጸልይ፤እንዲሁም ለጓደኞቻቸው፤ጎረቤቶቻቸው፤ለሚወዷቸው፤የክፍል ጓደኞቻቸው፤እና ለዓለም የክርስቶስን የምስራች ወንጌል ባገኙት አጋጣሚ የሚሰብኩ እና ሰዎችን እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ የሚረዱ እንዲሆኑ ጸልይ።

አንተ ለምትጸልይባቸው ስፍራዎች እና ህዝቦች መሀከል የሚገኙ ቤቶች የምስራቹን ወንጌል መስበኪያ፤የጸሎት ስፍራ እና ማህበረሰቡ እና ዓለም የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማበት ስፍራ እንዲሆን ጸልይ።**ሰዎች እግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉበት ስፍራ** ለጓደኞቻቸው፤ለጎረቤቶቻቸው፤ለወዳጆቻቸው፤ለስራ ባልደረቦቻው፤ለክፍል ጓደኞቻቸው እና ለዓለም ወንጌልን የሚሰብኩበት ስፍራ እንዲሆን ጸልይ።እድሎችን ባገኙ ጊዜ ሁሉ የምስራቹን ወንጌል የሆነውን ኢየሱስ የሚያካፍሉበት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መሰረታዊ የግል ህይወት፡የቤተሰብ

ህይወት፤የቤተክርስቲያን ህይወት፤ወንጌል ስብከት እና ደቀመዝሙር ማድረግ መርሆች መሰረት በዙሪያቸው ያሉትን የክርስቶስ ደቀመዝሙር የሚያደርጉበት ስፍራ እንዲሆን ጸልይ።
አንተ ለምትጸልይባቸው ስፍራዎች እና ህዝቦች የሚያገለግሉ አገልጋዮችን ሰዎችን የሚያንጽ እና ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆነውን ብቻ እንዲናገሩ እግዚአብሔር አንደበታቸው ላይ ጠባቂን እንዲያኖር ጸልይ።

**በኢየሱስ ስም እግዚአብሔር በልብህ በሚያስቀምጠው በማንኛውም አይነት ነገሮች እና ልዩ በሆነ በየጊዜው ወደ ልብህ በሚመጣው ነገር ጸልይ፤አሜን።**

WOULD YOU LIKE TO LIVE IN VICTORY

SO YOU CAN EFFECTIVELY SHARE JESUS WITH OTHERS?

WOULD YOU LIKE TO SHARE GOD’S MESSAGE WITH POWER?

WOULD YOU LIKE TO SEE LIVES REALLY CHANGE

AS YOU SHARE THE MESSAGE OF GOD’S LOVE?

WOULD YOU LIKE TO KNOW GOD'S PRINCIPLES FOR

SHARING THE STORY OF JESUS?

WOULD YOU LIKE TO KNOW

HOW TO TELL PEOPLE ABOUT GOD?

!!THEN THIS BOOK IS FOR YOU!!

Compiled by Bro. Henry Pulsifer
This is one of a series of booklets designed to help you *grow to know God* and fulfill His purpose for your life. Henry has experienced the victory that comes from knowing God for over 60 years; including God's healing from cancer as he walked with the cross. Since his healing he has traveled the world sharing *how to know God;* and helping others find blessings and success by *growing to know Him*, and fulfilling His purpose for their life.
Out of this experience he has compiled several learning guides that enable people to *grow to know God*, and understand how to live the basic Bible principles for blessings and success in life. This particular learning guide is designed to help you *grow to know God* as you tell people about Him each day. It can also be used to help you teach others, and is appropriate for individuals or groups.
COPYRIGHT 1999 ALL RIGHTS RESERVED
No part of this booklet may be reproduced without permission from the publisher. Except, portions may be reproduced if distributed free of charge.

Proper credit should be given for the source of the material.
PUBLISHED BY:
BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. Box 633
Grapevine, TX 76099 USA
Phone (228) 255-9251
Email basic@basicministries.com
Web page www.basicministries.com